# ልሳነ ጊዮርጊስ

ቅፅ 04 ቁጥር 515 መስከረም 29/2014 ዓ.ም



## ሃይደር ሸሪፋ

ከፋሲል ጋር በነበረው ጨዋታ የጨዋታው ኮከብ



## የአብስራ ተስፋዬ

ከአዳማ ጋር በነበረው ጨዋታ የጨዋታው ኮከብ



## ፀጋዬ መላኩ

ከባህርዳር ጋር በነበረው ጨዋታ የጨዋታው ኮከብ




## ፎሌምፓንግ ሜንሱ

ከመከላከያ ጋር በነበረው ጨዋታ የጨዋታው ኮከብ

Printed by Rehobot Printers Tel 0114 169027

# ልሳነ ጊዮርጊስ

ቅፅ 04 ቁጥር 515 ተጨማሪ መረጃዎችን በድረ ገፃችን ማግኘት ይችላሉ http://saintgeorgefc.com/blog/ መስከረም 29/2014 ዓ.ም



“የመንግስት ለውጥ ከመጣ ጊዜ ጀምሮ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አመራሮች ለስፓርቱ የሰጡት ክብደት ከፍተኛ ነው ፣ ይሄ የተጀመረው በኢንጅነር ታከለ ኡማ ጊዜ ነው ፣ እንዲህ ያለ ነገር ከዚህ ቀደም አይተነው የማናውቅ በመሆኑ ለእኛ እንግዳ ነገር ነው ፡ ፡ ክብርት ወ/ሮ አዳነች አበቤ ወደ ሃላፊነት ከመጡ ጊዜ ጀምሮ ያን ፈለግ በመከተል ለክለባችን ከፍተኛ ድጋፍ አድርገዋል” ገጽ...6

አቶ አብነት ገብረመስቀል
የቅዱስ ጊዮርጊስ ስፓርት ማህበር ፕሬዝዳንት



በአዲስ አበባ ከተማ ዋንጫ ላይ የተሰለፉት ወጣት ተጨዋቾቻችን ቅዱስ ጊዮርጊስ ከፍተኛ ተስፋ የሚጥልባቸው እንደሆኑ ሜዳ ላይ አሳይተዋል

# ርክሰ እንቀጽ

## ካጣነው ዋንጫ ይልቅ በወጣቶቻችን ያየነው ተስፋ የበለጠ ነው!!

በአዲስ አበባ ከተማ እግር ኳስ ፌዴሬሽን አዘጋጅነት መስከረም 15 ቀን 2014ዓ.ም በስምንት ተሳታፊ ቡድኖች መካከል ሲካሄድ የሰነበተው 15ኛው የአዲስ አበባ ከተማ ዋንጫ ቅዱስ ጊዮርጊስ በርካታ መልካም ነገሮችን ያገኘበት የውድድር መድረክ ነው፡፡ አንድም በቅድመ ውድድሩ ወቅት ያደረጋቸውን ዝግጅቶች ድክመትና ጥንካሬዎቹን ለመፈተሽ ምቹ አጋጣሚዎችን ያገኘበትና አቋሙን የፈተሸበት ነው፡፡ በሌላ በኩል በጨዋታው የተሳተፉ ታዳጊ ተጫዋቾቻችን ያሉበትን ወቅታዊ ብቃትና ችሎታ በአደባባይ ለማየት የተቻለበት ነው፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ ዋንጫ ላይ ወደ ዋናው ቡድን ያደጉ ወጣት ልጆቻችን እጅግ አስደናቂ የሜዳ ላይ እንቅስቃሴ አሳይተውናል፡፡ እውነትም ቅዱስ ጊዮርጊስ ዘመን ተሻጋሪ እና በትውልዶች ቅብብሎሽ የጸና ክለብ እንደሆነ ወጣቶቹ ያሳዩት እንቅስቃሴ ምስክር ነው ለማለት ይቻላል፡፡ ወጣቶቹ በሁሉም ጨዋታዎች ላይ ያሳዩት እንቅስቃሴ የሚያስደስት ይልቁንም ቅዱስ ጊዮርጊስ በሌሎች ተጫዋቾች ግዥ ላይ ጥገኛ ከመሆን ይልቅ የራሱን ታዳጊዎችና ወጣቶች በስፋት አሳድጎ ቢጠቀምና እድሉን ቢሰጥ ይበልጥ የሚጠቀም ይበልጥ የሚያተርፍ ቅዱስ ጊዮርጊሳዊ ፍቅርና ቡድናዊ አንድነትን መልሶ ለመፍጠር እንደሚቻል የታየበት አጋጣሚ ነው፡፡ ቅዱስ ጊዮርጊስ ብዙ አቅሞች ያሉት ከራሱ አልፎ ለሌሎች የሚተርፍ ትልቅ ክለብ ነው፡፡

ከሀገራችን ክለቦች በተለየ ራሱ የታዳጊዎች ማሰልጠኛ አካዳሚ የገነባ በርካታ እምቅ አቅምና ችሎታ ያላቸው ታዳጊና ወጣቶችን ያሰባሰበ የተጫዋቾች ሃብታም የሆነ ክለብ ነው፡፡ በታዳጊዎቹ ላይ ያየነው ተስፋ ሰጪ የሆኑ እንቅስቃሴዎች ወደ ፊት ቅዱስ ጊዮርጊስ በብሄራዊ ቡድን ደረጃ ውጤታማ እና ተጽእኖ ፈጣሪ ተጫዋቾች መፍጠሩን እንዳላቆመ ያመላከተ ነበር፡፡

በዚህ የውድድር መድረክ ላይ ካለፉት ዓመታት በተሻለ ለቁጥራቸው የበረከቱ ወጣት ተጫዋቾችን ማሳተፍ ተችሏል፡፡ ሁሉም በተሰለፉባቸው ጨዋታዎች አስደናቂ በሆነ ሁኔታ ብቃታቸውን አሳይተዋል በቀጣይ ውድድሮችም ልምድ ካላቸው ተጫዋቾች ጋር የበለጠ ማቀናጀትና ማዋሃድ ከተቻለ የተሻለ ነገር እንደሚያሳዩን እናምናለን፡፡

"አስተውሎ የሚጓዝ ብዙ ርቀት ይሄዳል" እንደሚባለው አሁንም ለወጣቶቻችን የበለጠ ትኩረት መስጠት ከነርሱ ጋር ሳይታክቱ በመስራት ቅዱስ ጊዮርጊስን ብዙ ርቀት ወደ ፊት ይዘውት እንዲጓዙ ሁኔታዎችን ማመቻቸት እንደሚገባ እናውቃለን፡፡ ተስፋችን በወጣቶች ላይ መሆን አለበት ሁል ጊዜም ባልተቋረጠ ሁኔታ ወጣቶችን የመተካት አስተማማኝ የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት የቅዱስ ጊዮርጊስ ተስፋ በወጣቶች ላይ የተመሰረተ እንዲሆን ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

ስለሆነም ተተኪዎች ከታላላቆቹ ጋር እየተሰባጠሩ ብዙ ልምድ እንዲያገኙ ሰፊ እድል ማመቻቸትና ክለባችን የማይነጥፍ የተተኪ ወጣቶች ክለብ እንዲሆን የበለጠ መስራት ይገባል፡፡ በ15ኛው የአዲስ አበባ ከተማ ዋንጫ ካጣነው ዋንጫ ይልቅ በወጣት ተጫዋቾቻችን ላይ ያየነው ተስፋ እጅጉን የሚልቅ እንደሆነም ተረድተናል፡፡ ምንጊዜም ጊዮርጊስ!

# “ወጣቶቹን ልምድ ካላቸው ተጫዋቾች ጋር በማዋሃድ ውጤታማ እንዲሆኑ ማድረግ ይቻላል”

### የፈረሰኞቹ ምክትል አሰልጣኝ ዘሪሁን ሸንገታ

የፈረሰኞቹ ምክትል አሰልጣኝ ዘሪሁን ሸንገታ ቡድኑ በ15ኛው የአዲስ አበባ ከተማ ዋንጫ ያደረጋቸውን ጨዋታዎችና ወደ ዋናው ቡድን ያደጉ ወጣት ተጫዋቾች የነበራቸውን የሜዳ ላይ እንቅስቃሴ በተመለከተ ከልሳነ ጊዮርጊስ ጋር አጠር ያለ ቆይታ አድርገዋል፡፡ መልካምቆይታ!



**ልሳነ ጊዮርጊስ፡- የአዲስ አበባ ከተማ ዋንጫ ውድድር ቆይታ ምን ይመስላል?**

**አሰልጣኝ ዘሪሁን፡-** በጣም ጥሩ ነው ከምንጠብቀው በላይ በአጭር ጊዜ ውስጥ የሰሩትን በተግባር ያሳዩበት እና የተጫወቱበት መንገድ በጣም አስደሳች እና ጥሩ ምላሽ ያገኘንበት ነው፡፡ ጥቂት ተጫዋቾቻችን ለብሄራዊ ቡድን የተጠሩ ቢኖሩም እጃችን ላይ ባሉት ወጣቶች ጨዋታውን ለማሸነፍ እና የተሻለ ነገር ለማሳየት ከፍተኛ ጥረት አድርገናል፡፡ በተጨማሪም በጨዋታው ወቅት ማን ከማን የተሻለ እንደሆነ አጠቃላይ እንቅስቃሴያቸውን ለማየትና ለመገንዘብ ዕድል ያገኘንበት አጋጣሚ ነበር፡፡

**ልሳነ ጊዮርጊስ፡- በአዲስ አበባ ከተማ ዋንጫ በተደረጉት አራት ጨዋታዎች ያሰባችሁትን አሳክታችኋል ማለት ይቻላል?**

**አሰልጣኝ ዘሪሁን፡-** እውነቱን ለመናገር መቶ በመቶ አሳክተናል ማለት ባንችልም የሲቲ ካፑ ጨዋታ ራሳችንን መፈተሻ እንደመሆኑ የጎደሉን ነገሮች ነበሩ እንዲያም ሆኖ ግን በጣም ተስፋ ሰጪ የሆኑ እንቅስቃሴዎችን ሜዳ ላይ አይተናል በዚህም ወደፊት ውጤታማና ተፅዕኖ ፈጣሪ የሆኑ ተጫዋቾች እንደሚፈጠሩ ያየንበትም ነበር፡፡

**ልሳነ ጊዮርጊስ፡- ከታች ወደ ዋናው ቡድን ያደጉ ተጫዋቾቻችን እንቅስቃሴ እንዴት ነበር?**

**አሰልጣኝ ዘሪሁን፡-** ካለፉት ዓመታት በተሻ መልኩ ቁጥራቸው በርከት ያሉ ወጣት ተጫዋቾችን በውድድሩ ላይ አሳትፈናል ልጆቹ በተሰለፉባቸው ጨዋታዎች ሁሉ አስደናቂ በሆነ ሁኔታ ብቃታቸውን አሳይተዋል ልምድ ያገኙበት ጨዋታ ነው፡፡ በቀጣይ ውድድሮችም በርትተው ከሰሩ ልምድ ካላቸው ተጫዋቾች ጋር ተዋህደው የተሻለ ነገር ያሳዩናል የሚል ጽኑ እምነት አለኝ፡፡

**ልሳነ ጊዮርጊስ፡- በጨዋታው ወቅት በቡድኑ ላይ የታዩ ክፍተቶች እና ጉድለቶች ምን ነበሩ?**

**አሰልጣኝ ዘሪሁን፡-** ምርጥ ብቃት ላይ የሚገኙና የተሻሉ ተጫዋቾቻችን ብሄራዊ ቡድኑ ባደረገው ጥሪ ምክንያት ከኛ ጋር አይደሉም አራት ተጫዋቾቻችንም ጉዳት ላይ ነበሩ አሁን አገግመው ልምምድ እየሰሩ ይገኛሉ፡፡ በቀጣይ ጉድለቶቻችንን አርመን የሄዱትም ሲመለሱ የተሻለ ነገር እናሳያለን የሚል እምነት አለኝ፡፡

**ልሳነ ጊዮርጊስ፡- ከአዲስ አበባ ከተማ ዋንጫ ጨዋታ ምን ትምህርት ተገኘ በቀጣይስ ምን እንጠብቅ?**

**አሰልጣኝ ዘሪሁን፡-** ትልቁ ነገር የአዳጊ ወጣቶች ቅንጅት እና አንድነት እንዲሁም ለብሄራዊ ቡድን የተጠሩ ተጫዋቾች ወደ ቡድናችን ሲቀላቀሉ እስካሁን ያደረግነውን እንቅስቃሴ ጨምረንበት አሁን ያለንን ቅርፅ አስተካክለን ከፊታችን ለሚጠብቁን የፕሪሚየር ሊጉ ውድድሮች በጥሩ ሁኔታ እየተዘጋጀን እንገኛለን፡፡

**ልሳነ ጊዮርጊስ፡- በመጨረሻም የሚያስተላልፉት መልዕክት?**

**አሰልጣኝ ዘሪሁን፡-** እስካሁን በነበረን የአዲስ አበባ ከተማ ዋንጫ ጥሩ ነገሮችን አይተናል በቀጣይም ችግሮቻችንን ለይተን በማውጣት የተሻለ የውድድር ጊዜ እንደምናሳልፍ ሙሉ እምነት አለኝ፡፡ ከጎናችን ሆነው ለደገፉን እና ወደፊትም አብረውን ለሚሆኑ ደጋፊዎቻችን ከፍ ያለ ክብር አለኝ፡፡

**ልሳነ ጊዮርጊስ፡- አመስግናለሁ፡፡**
**አሰልጣኝ ዘሪሁን፡-** እኔም አመስግናለሁ፡፡

**አሳታሚ፡- የቅዱስ ጊዮርጊስ ስፖርት ማኅበር**
**ኤዲቶሪያል ቦርድ አባላት፡- ሚሊዮን አለሙ፣ ዮሐንስ በርናባስ፣ ብርሃኑ ተስፋዬ**
**ዋና አዘጋጅ፡- ሰኪና ሲራጅ**
**ረዳት አዘጋጅ፡- አየነው አዲስ**
**ዝግጅት አስተባባሪ፡- ታሪኬ ቀጭኔ**
አምደኛ
- ካፑካ ሣንጆርጅ
**የጋዜጣ ስርጭት፡-**
**እንግዱ ወርቁ**
**ህትመት፡- ርኆቦት**
**አታሚዎች**
**ፎቶ፡- መኮንን ወሎ**
**የዝግጅት ክፍሉ አድራሻ፡-**
**ቂርቆስ ክፍለ ከተማ**
**ወረዳ፡-4**
**የቤት ቁጥር፡-096**
**ስልክ፡- +1114663679**
**ፖ.ሣ.ቁ፡- 18753**



የክለባችን...
ከገፅ 6 የዞረ

አሰልጣኝ ነው ጠንካራ ነው ሁሉንም በእኩል አይን ነው የሚያየው ስለዚህ እኔ የዲሲፒሊን ችግር መቶ በመቶ ይቀረፋል ባልልም ጊዮርጊስ ውስጥ ያን ቀይ መስመር ያለፈ እንደሚባረር ስለሚያውቅ ከ 95 በመቶ የበለጠ ልጆቻችን ጥንቁቅ ናቸው ብዬ ነው የማስበው ይሁንና በቅዱስ ጊዮርጊስ በዲሲፒሊን ጥፋት የተቀጣ ተጫዋች ለብሄራዊ ቡድን ሲመረጥ የበለጠ በክለብ ሳይሆን በሀገር ደረጃ ጥፋት እስከሚሰራ መጠበቅ በጣም ያሳዝናል አንዳንድ ግዜ ሞኝ በራሱ ብልጥ በሰው ይማራል እንደሚባለው እንዲህ አይነት ባህሪ ያላቸው ተጫዋቾች ብሄራዊ ቡድን ዉስጥ ይቀየራሉ ማለት ዘበት ነው፡፡

ስለዚህ እስከሚቀየሩ ድረስ ከዚህም ከዛም ቅጣቱ ሲበዛ ለሌሎቹም ትምህርት ነው፡፡ ዛሬ ክለቡ ውስጥ ጥፋት የሰራ ብሄራዊ ቡድን አባል ሆኖ የሚመረጥ ከሆነ ክለባቸው ውስጥ እንደፈለጉ ይሆናሉ ስለዚህ እንደ አሰራር ሁሉም የስፖርት ቤተሰቦች ውስጣቸውን እየፈተሹ የዲሲፒሊን ነገር እርማት መውሰድ ይገባል ነገ የከፋ ጥፋት ሊፈጽም ይችላል፡፡

**ልሳነ ጊዮርጊስ፡- ከዚህ ቀደም የነበረው የአዲስ አበባ ከተማ አስተደደር ከክለባችን እና ከአዲስ አበባ ክለቦች ጋር የፈጠረው ግንኙነት እንዴት ነበር?**

**አቶ አብነት፡-** የመንግስት ለውጥ ከመጣ ጀምሮ የብልፅግና አመራሮች ለስፖርቱ የሰጡት ክብደት በተለይ ለወጣቱ ከፍተኛ ነው ይሄ የተጀመረው በኢንጅነር ታከለ ኡማ ጊዜ ነው እሳቸው ወጣቱን በችግኝ ተከላውም ቀርቦ በማነጋገርም የስፖርት ማዘውተሪያ ቦታ በመስጠትም በጣም ብዙ ውለታ ውለዋል ለመጀመሪያ ጊዜ ከመንግስት አካላት ህዝባዊ ክለብ ጋር የተቀራረቡ ሰው ናቸው፡፡

ከዚህ በፊትም ምስጋና አቅርቢያለሁ በዚህ አጋጣሚ አሁንም ደግሜ ላመሰግናቸው እወዳለው፡፡ ክብርት ወ/ሮ አዳነች አበቤ ወደ ሃላፊነት ከመጡ ጊዜ ጀምሮ ያን ፈለግ በመከተል ለክለባችን ከፍተኛ ድጋፍ አድርገዋል የአዲስ አበባ ህዝባዊ ክለብ እንደመሆናችን መጠን እያደረጉ ያሉት ከፍተኛ እገዛ ምንጊዜም ከልባችን የማይወጣ ነው፡፡

ከእኛ ጋር ለመስራት ያላቸውን ቁራጥነታት ከዚህ በፊት አይተናል እንዲህ ያለ ነገር ከዚህ ቀደም አይተነው የማናውቅ በመሆኑ ለእኛ እንግዳ ነገር ነው፡፡ መንግስት ህዝባዊ ክለቦችን መደገፉ ወጣቶችን አልባሌ ቦታ እንዳይውሉ ትልቅ ነገር በመሆኑ የሚያስመሰግን ነው ለማለት እችላለሁ ለወደፊቱም በኛ በኩል በስፖርቱ ልማት ዙሪያ አብረን ለመስራት ዝግጁ ነን፡፡

**ልሳነ ጊዮርጊስ፡- የደጋፊውን ስሜትና ፍቅር እንዴት ይገልጹታል?**

**አቶ አብነት፡-** የምገልጽበት ቃላቶች የሉኝም እኔ ሜዳ ውስጥ ስገባ ራሴን አላውቀውም ሁሉም ደጋፊዎቻችን ገብተው ጨዋታዎችን እንዲመለከቱና ስታዲየሙ ከአፍ እስከ ገደፉ ጢም ብሎ እንዲሞላ ነው የምፈልገው ፈጣሪ ጠብቆን ለወደፊቱም አብረን ብዙ ነገሮችን የምናይ ነው የሚሆነው፡፡

**ልሳነ ጊዮርጊስ፡- ለነበረን ጊዜ አመሰግናለሁ፡፡**
**አቶ አብነት፡-** እኔም ለተሰጠኝ እድል አመሰግናለሁ፡፡

# በ15ተኛው የአዲስ አበባ ከተማ ዋንጫ ከፋሲል ከነማ ጋር በነበረው ጨዋታ ድንቅ ብቃቱን በማሳየቱ የጨዋታው ኮከብ የነበረው የፈረሰኞቹ አምበል ከሃይደር ሸረፋ ጋር ያደረግነውን አጭር ቆይታ እነሆ!



**ልሳነ ጊዮርጊስ፡- በአዲስ አበባ ከተማ ዋንጫ የነበራችሁ ቆይታ እንዴት ነበር ?**

**ሃይደር፡-** እንደሚታወቀው የሲቲ ካፕ ውድድር ከዝግጅት ምዕራፍ በኋላ የሚደረግ ውድድር እንደመሆኑ በውድድሩ ራሳችንን የምንገመግምበት ክፍተቶቻችንን የምንለይበት ተጫዋቾች የሚሞከሩበት ምን አይነት ሲሲተም ያዋጣኛል ብሎ አሰልጣኙ የሚሞክርበት ለፕሪሚየር ሊጉ ዝግጅት የምንናደርግበት ብዙ ታዳጊ ወጣቶች የተሳተፉበት፣ጥሩ የአጨዋወት እንቅስቃሴ ያደረግንበ ስለሆነ ጥሩ ግዜን አሳልፈናል ብዬ አስባለሁ፡፡

**ልሳነ ጊዮርጊስ፡- የአምበልነቱ ሚና እንዴት ተወጣህው? ከታዳጊ ወጣቶች ጋር የነበራችሁ ውህደት ምን ይመስል ነበር?**

**ሃይደር፡-** ቅዱስ ጊዮርጊስ ትልቅ ክለብ ነው፣ በማንኛውም ውድድር ላይ ለክለቤ አምበል በመሆኔ ትልቅ ኩራት ይሰማኛል፡፡

ታዳጊዎቻችን ደግሞ ብዙ ሰዎች እንዳዩዋቸው ነገ ቡድን መምራት የሚችሉ ጥሩ ብቃት ያላቸው ታዳጊዎች የታዩበት ውድድር ነው፡፡ ብዙ ልጆችን መጥቀስ ይቻላል፣ እነ ፀጋዬ፣ አልአዛር፣ ሻሂዱ ጥሩ ብቃታቸውን ካሳዩት ውስጥ ይጠቀሳሉ፡፡ ልጆቹን አምናም ዘንድሮም አውቃቸዋለው፣ ከዚህ የተሻለ ብቃት እንዳላቸውም አውቃለሁ፣ ወደፊት ይሄን ብቃታቸውን አጠናክረው ትልቅ ደረጃ እንደሚደርሱ አሳይተዋል፡፡እኛም እንደ ሲኒየርነታችን እየተቆጣን እያበረታታን እየደገፍናቸው እና እያገዝናቸው እንገኛለን፡፡

**ልሳነ ጊዮርጊስ፡- በውድድሩ ጥንካሪያችሁና ድክመታችሁ ምን ነበር?**

**ሃይደር፡-** እንደ አጨዋወት ብዙ ድክመቶች ነበሩብን ከጥንካሬያችን ስጀምር በህብረት መጫወታችን መደማመጣችን በጨዋታዎች ጎል ማስቆጠራችን ጥሩ ነበር በጨዋታ ምንም አይነት ጎል አልተቆጠረብንም፡፡ ከመከለከያ ጋር በነበረው በመጨረሻው ጨዋታ ላይ ያገኘናቸውን አጋጣሚዎች መጠቀም አለመቻላችን ትልቁ ድክመታችን ነው፡፡

**ልሳነ ጊዮርጊስ፡- በቀጣይ ከሚደረጉት የፕሪሚየር ሊግ ጨዋታዎች ምን እንጠብቅ ?**

**ሃይደር፡-** ከአላህ ጋር ጥሩ ነገር ጠብቁ፣ ለብሄራዊ ቡድን የሄዱት ጓደኞቻችን ሲመለሱ ካለፈው ተሻለ ተዋህደን ከአሰልጣኞች ጋር በመተባበር ያሉብንን ክፍተቶች እያረምን ጥሩ የአጨዋወት ስልት ይዘን እንቀርባለን የሚል ትልቅ እምት ነው ያለኝ፡፡

**ልሳነ ጊዮርጊስ፡-በመጨረሻም የምታስተላልፈው መልዕክት ካለህ?**

**ሃይደር፡-**ያለፈው አመት ያለ ደጋፊ እንደተጫወትን ይታወቃል፣ ደጋፊዎቻችን ለኛ ብርታት ስለሆኑ ያለደጋፊ ሜዳ ውስጥ ገብቶ መጫወት ከባድ ነገር ነው፣ አሁን ደጋፊዎች ስቴዲየም ገብተው ጨዋታ ማየት ጀምረዋል በዚሁ አጋጣሚ እንደ ሁልጊዜው ደጋፊዎቻች ከጎናችን እንዲሆኑ እጠይቃለሁ።

## የ2014 ዓ.ም የኢትዮጵያ ቤትኪንግ ፕሪሚየር ሊግ የመጀመሪያ ዙር አምስት የቅዱስ ጊዮርጊስ ጨዋታዎች መርሃ ግብር

| የጨዋታ ቀን | ተጋጣሚዎች | የጨዋታ ሰዓት | ቦታ |
|---|---|---|---|
| ጥቅምት 10/2014 | ሰበታ ከተማ ከ ቅዱስ ጊዮርጊስ | 1፡00 | ሃዋሳ ዩኒቨርሲቲ ሜዳ |
| ጥቅምት 16/2014 | ቅዱስ ጊዮርጊስ ከ ኢትዮጵያ ቡና | 1፡00 | ሃዋሳ ዩኒቨርሲቲ ሜዳ |
| ጥቅምት 22/2014 | ድሬዳዋ ከነማ ከ ቅዱስ ጊዮርጊስ | 9፡00 | ሃዋሳ ዩኒቨርሲቲ ሜዳ |
| ህዳር 15/2014 | መከላከያ ከ ቅዱስ ጊዮርጊስ | 1፡00 | ሃዋሳ ዩኒቨርሲቲ ሜዳ |
| ህዳር 20/2014 | ቅዱስ ዮርጊስ ከ ሲዳማ ቡና | 1፡00 | ሃዋሳ ዩኒቨርሲቲ ሜዳ |







# ገፀ - መንግስቱ ወርቁ

"እኔ ለቅዱስ ጊዮርጊስ
ሁሉ ነገሬን እሰጣለሁ"
መንግስቱ ወርቁ



## የክለባችን ፕሬዝዳንት አቶ አብነት ገብረመስቀል ያለፈው የ2013 የውድድር ዓመትና በወቅታዊ የክለባችን ሁኔታ እንዲሁም በወጣት ተጫዋቾች ዙሪያ ከስፖርት ማኅበራችን ሚዲያ ጋር ቆይታ አድርገዋል፡፡ መልካም ንባብ !



**ልሳነ ጊዮርጊስ፡- በቅድሚያ ለቃለመጠይቁ ፈቃደኛ ስለሆኑ አመሰግናለሁ?**
**አቶ አብነት፡-** እኔም እድሉን ስላገኘሁ አመሰግናለሁ!

**ልሳነ ጊዮርጊስ፡- በቅድሚያ 2013 ዓ.ም የወድድር ዓመትና በአጠቃላይ ያሳለፍነው ዓመት እንዴት ነበር?**
**አቶ አብነት፡-** 2013 ለኛ እና ለሀገራችን ጎዶሎ ዓመት ነበር በብዙ መልኩ እኛ እንዳሰብነው እግርኳሳችን ወደ ፊት ሊሄድ አልቻለም እንደ ሀገርም በየቦታየው በነበረው ረብሻ ምክንያት ብዙ ወገኖቻችን ህይወታቸውን ያጡበት እና የተጎዱበት በመሆኑ ብዙ ችግሮችን ተቋቁመን ነበር፣ ያሳለፍነው ነው፡፡ ደጋፊዎቻችን በየቦታው ጉዳት የደረሰባቸውን ወገኖች ለመደገፍ ያቅማቸውን ያህል በቁሳቁስና በገንዘብ ድጋፍ በማድረግ አለኝታነታቸውን አሳይተዋል፡፡ እንዲህ ያለው ተግባር እጅግ በጣም የሚያስመሰግን ነው፡፡

ቅዱስ ጊዮርጊስ ባለፈው የውድድር ዓመት አጀማመሩ ተስፋ ሰጪ የነበረ ቢሆንም ወደ ኋላ ላይ ግን እየዋዠቀ አሉ የተባሉት ትልልቅ ተጫዋቾች ሁሉ ሜዳ ላይ ቄጠማ ሆነው ሲታይ ችግር እንዳለ ያሳየ ነበር፡፡ አንደኛ በተጫዋቾች መካከል ፍቅር ያለ አይመስልም ዋናው የቅዱስ ጊዮርጊስ ጥንካሬ ፍቅር ነበር ሌላው ከፍተኛ የዲሲፒሊን ችግር ነበር ያን ሁሉ ችግር ተቋቁሞ መቀጠል ለክለባችን አስቸጋሪ ስለነበር ለማስተካከል ቆራጥ እርምጃ መውሰድ ነበረብን ቦርዱ በአስቸኳይ ስብሰባ በማድረግ ለቅዱስ ጊዮርጊስ ፍቅር ያላቸውን ተጫዋቾች ብቻ በመተው ችግር ፈጣሪዎችን በመለየት እንዲሰናበቱ አድርጓል፡፡ ያለፈው ዓመት ትምህርት ሰጥቶን ያለፈ በመሆኑ በተቻለ መጠን ለ2014 የውድድር ዓመት በከፍተኛና ጥብቅ ዲሲፒሊን እንድንዘጋጅና የበለጠ እንድንጠናከር እንዲሁም አንድነታችን እንዳይሸረሸር ከፍተኛ ትኩረት ሰጥተን ዝግጅት ስናደረግ ቆይናል፡፡

ቅዱስ ጊዮርጊስን እንደስሙ ይዘን ወደፊት ለመቀጠል አሁንም ዲሲፒሊንና ጠንካራ ስራ ይጠብቀናል፡፡ በክለባችን አሸናፊነት ዙሪያ አንደራደርም ፣ ማሸነፍ ባህላችን ቢሆንም ላለፉት አራት ዓመታት በተለያዩ ምክንያቶች ከዋንጫ ርቀናል፡፡ በ2013 ዓ.ም የውድድር ዓመት ሰበብ ሳንፈጥር ዋንጫውን የማንሳት የተሻለ ዕድል እያለን በራሳችን ድክመት ዋንጫውን አሳልፈን ሰጥተናል፣ ከየትኛውም ውድድር ውጪ እንድንሆን ያደረጉት የራሳችን ልጆች ናቸው፡፡

ስለሆነም ካለፈው ዓመት ተምረን በዚህ ዓመት ከአሰልጣኝም ምልመላ ጀምሮ ከተጫዋቾች አቀጣጠር ጀምሮ በወጣት መገንባት እንዳለበት ታዳጊ ወጣቶችን ወደ ላይ መምጣት እንዳለብን አስበን ተግባራዊ በማድረጋችን እና ሌሎች ተያያዥ ስራዎችን ሰርተን ነው በዚህ ዓመት ብቅ ያልነው፡፡

**ልሳነ ጊዮርጊስ፡- ከወጪ አንፃር ከፍተኛ ገንዘብ የፈሰሰበት የቅድመ ውድድር ጊዜ እንዳሰለፈ ይታወቃል ከዚህ አንፃር እርስዎ ምን ይላሉ?**

**አቶ አብነት፡-** ቅዱስ ጊዮርጊስ ገንዘብ ከሰማይ አይፈስለትም የብዙ ሰው ፊት ገርፎን ነው የምንሰበስበው፣ ጥሩ ቲምና አሪፍ ውጤት ስለፈለግን ካለወጪ ስፖርቱ አይካሄድም ስለሆነም ከፍተኛ ወጪ ነው የምናወጣው ፣ 10 አዳዲስ ተጨዋቾች ማምጣት ማለት ከፍተኛ የሆነ ብርነው የሚጠይቀው፣ እነዚህን ተጫዋቾች አንድ ወር ገደማ ካምፕ ውስጥ ዘግተህ ማዘጋጀት ከባድ ነገር ነው፡፡ በወር ለምግብ ከ 1 ነጥብ 5 እስከ 2 ሚሊዮን ብር ገደማ ወጪ እናወጣለን ህክምና በተመለከተ ቶሎ ቶሎ ክትትል ይደረጋል፣ ነርስ አለ፡፡

ወጌሾች አሉ፣ ለነዚህ ሁሉ የምናወጣው ወጪ ቀላል አይደለም፡፡ የሚያስደስተው ነገር ቅድመ ዝግጅቱ ላይ ያፈሰስነው ኢንቨስትመንት መልሶ እየከፈለን ነው፡፡ አንደኛ ታዳጊዮች ከፍ እንዲሉ ማድረግ ሁለተኛው ከውጭ የሚመጡ ተጫዋቾች በዕድሜ አነስተኛ ቢሆኑም በችሎታ ብስለት ያላቸውን ተጫዋችን ነው ያሰባሰብ ነው፡፡ ከውጪ አገር ወደ ክለባችን የተቀላቀሉ ተጫዋቾች የብሄራዊ ቡድን ተጫዋቾች ናቸው፡፡ ቀደም ሲል እንዳልኩት ትንሽ ብር ከከፈልን ደህና ተጫዋች ማግኘት አንችልም፣ ስለዚህ ቀበቷችንን ጠበቅ አድርገንና መስዋትነት ከፍለን ነው ይሄ ቅድመ ዝግጅት የተሳካ እንዲሆን ያደረግነው፡፡

**ልሳነ ጊዮርጊስ ፡- ወጣቶችን በብዛት እና በላቀ ቁጥር ማሳደግ ለተወሰነ ዓመታት ቁጥር ቀንሶ እንደነበር ይነሳል ዘንድሮ ግን አስደናቂ በሆነ ሁኔታ እጅግ ፍሬ ያላቸውን ታዳጊዎች ለመመልከት ችለናል ታዳጊዎችላይ ያለው ምልከታ ምን ይመስላል?**

**አቶ አብነት፡-** ተስፋችን ወጣቶች ላይ ነው ትልልቆቹ በወቅቱ ወጣት በነበሩበት ሰዓት ሰርተዋል፣ እግር ኳስ መጫወት ደግሞ ድካም አለው፣ ተተኪ ደግሞ ማዘጋጀት አለብን ዘላለም ተጫዋቾች በመግዛት አንችለውም ስለዚህ እነዚህ ተተኪዎች ዕድል ከተሰጣቸው ከትልልቆቹ ጋር እየተደባለቁ ልምድ እንዲያገኙ ማድረግ ይገባል፡፡

ስለዚህ ወጣቶቹ ያጡት ዕድል ነው፣ ዕድል እንዲሰጣቸው አድርገናል፡፡ ከዛ ውጪ ራሳቸው ተጫዋች መሆናቸውን በችሎታ በጉልበትም በሁሉም ነገር ማስመስከር እንዲችሉ ጠንክሮ መስራት አለባቸው፡፡ በዚህ የዝግጅት ወቅት ያየነው ተስፋ በጣም ትልቅ ነው፡፡

10 ተጫዋቾችን አሳድገን ሶስት እና አራት አገኘን ማለት በጣም ጥሩ ውጤት ነው፡ስለዚህ ይሄ ነገር እንዲለመድ እንፈልጋለን፡፡ በዚሁ አጋጣሚ የነሱ አሰልጣኞች በየሳምንቱ እየተቀያየሩ ከዋናው ቡድን ጋር እንዲያሰለጥኑ አድርገናል እነ ሳሚ ፍሌክስ፣ ደረጄ፣ ከዘሪሁን ጋር በመሆን እንዲሁም ከዋና አሰልጣኝ ጋር በመሆን ልምድ እንዲያገኙ ተደርጓል ዓመቱም የተሳካ ዓመት ይሆናል የሚል እምነት አለን እንቅስቃሴውም ጥሩ ነው፡፡

በቅድመ ዝግጅቱ ወቅት አምስት ጊዜ ቢሾፍቱ በመሄድ ልምምዳቸውን እና የወዳጅነት ግጥሚያቸውን አይቻለሁ አመርቂ የሆነ ኳስ ነው የሚጫወቱት ነገር ግን ኳስ ነውና አንዱ ጨዋታ ከሌላው ጨዋታ ጋር አንድ ላይሆን ይችላል እንደዚህ አይነት ነገሮች ሲኖሩም በልምምድ እና በጨዋታ ወቅት ልምዶች ይገኛሉ፡፡ ኳስ ላይ ራስህን ካላሻሻልክና ከጊዜ ጋር ካልታገልክ እግር ኳሱ ልትቆይ አትችልም ስለዚህ ወጣቶቹ እግር ኳሱ ላይ ብቻም

> "ተስፋችን ወጣቶች ላይነው ትልልቆቹ በወቅቱ ወጣት በነበሩበት ሰዓት ሰርተዋል እግርኳስ መጫወት ደግሞ ድካም አለው ተተኪ ደግሞ ማዘጋጀት አለብን ዘላለም ተጫዋች በመግዛት አንችለውም ስለዚህ እነዚህ ተተኪዎች ዕድል ከተሰጣቸው ከትልልቆቹ ጋር እየተደባለቁ እድል ያገኛሉ፡፡"

ሳይሆን ስነ ልቦናው ላይም መበርታት አለባቸው፡፡ አዳነ ግርማ ቡድን መሪ ሆኖ ሲመጣ አንዱ ስራው በስነ ልቦናው ዙሪያ ልጆቹ ላይ እንዲሰራ በማሰብ ነው፡፡ እነ ዘሪሁን ልጆች ጊዮርጊሳዊ እንዲሆኑ የሚያደርጉት ጥረት አለ ተስፋ የሚሰጡ ልጆች አሉ አንድነታቸው ፍቅራቸው በጣም ደስ የሚል ሁኔታ ላይ ነው ያለው፡፡

**ልሳነ ጊዮርጊስ፡- በ2014 ዲሲፒሊን ላይ ምን አቋም ይዘን እንቀጥላለን?**
**አቶ አብነት፡-** አቋማችን አንድ እና አንድ ነው ዲሲፒሊን ያላከበረ ሰው በሩ ክፍት ነው መሄድ ይችላል ከማንም ጋር በዚህ ጉዳይ ላይ አንደራደርም አሰልጣኙም በጣም ትልቅ

ወደ ገፅ 7 ዞሯል



# የደጋፊዎች እና የ BGI ገጽ

ይህ ጋዜጣ ጥራቱን ጠብቆ እንዲወጣ ቢጂአይ ለሚያደርገው ትብብር ምስጋናችን ከፍ ያለ ነው፡፡

# 15ኛው የአዲስ አበባ ከተማ ዋንጫ አጭር ዳሰሳ



መስከረም 15 ቀን 2014 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ እግር ኳስ ፌዴሬሽን አዘጋጅነት በአበበ ቢቂላ ስታዲየም በተጀመረው እና ስምንት ቡድኖችን ባሳተፈው 15ኛው የአዲስ አበባ ከተማ ዋንጫ ፈረሰኞቹ ካደረጓቸው አራት ጨዋታዎች መካከል ሶስቱን ሲያሸንፉ በአንዱ ተሸንፈው ከዋንጫ ውድድር ውጭ ሆነዋል፡፡ በዚህ ጨዋታ ቅዱስ ጊዮርጊስ ካሰለፋቸው ተጫዋቾች መካከል አምስት ተጫዋቾች ማለትም ሃይደር ሸረፋ ፣ጋዬ መላኩ፣ ፍሪምፖንግ ሜንሱ፣ አላዛር ሳሙኤል እና ቶጓዊው እስማኤል አውሮ ጎል ማስቆጠር ችለዋል፡፡

ፈረሰኞቹ በዚህ ጨዋታ ላይ በአብዛኛው ወደ ዋናው ቡድን በቅርቡ ያደጉ ወጣቶችን በማሰለፍ የተጫወቱ ሲሆን አዳጊዎቹ ድንቅ የሚባል የሜዳ ላይ እንቅስቃሴ ያሳዩበት አጋጣሚ ነበር፡፡ በዚህ ጨዋታ ከተሰለፉት የቡድኑ አባላት መካከል ሃይደር ሸረፋና ጋዬ መላኩ እያንዳንዳቸው ሁለት ጎሎችን መረብ ላይ አሳርፈዋል፡፡ በአጠቃላይ ቅዱስ ጊዮርጊስ አራት ጨዋታዎችን አድርጎ ሰባት ጎሎችን መረብ ላይ አሳርፏል፡፡

መስከረም 17 ቀን 2014 ዓ.ም በነበረው የምድቡ የመጀመሪያ ቀን ጨዋታ ፋሲልን ያስተናገዱት ፈረሰኞቹ ሃይደር ሸረፋና አልአዛር ሳሙኤል በጨዋታ ካስቆጠሯቸው ጎሎች ባሻገር እስማኤል አውሮ አንድ ጎል በቅጣት መረብ ላይ በማሳረፍ በድምሩ የአምናውን የፕሪሚየርሊግ አሸናፊ ፋሲልን 3 ለባዶ በሆነ ውጤት አሸንፈዋል፡፡ የእለቱ የጨዋታው ኮከብ የነበረው ሃይደር ሸረፋም ከአዲስ አበባ እግር ኳስ ፌዴሬሽን የተዘጋጀለትን የ12 ሺ ብር እና ልዩ ሽልማት ተቀብሏል፡፡ መስከረም 20 ቀን 2014 በነበረው የምድቡ ሁለተኛ ጨዋታ አዳማን ያስተናገዱት ፈረሰኞቹ በየአብስራ ተስፋዬ ብቸኛ ጎል አዳማን አንድ ለ ባዶ በሆነ ውጤት በማሸነፍ መሪነታቸውን አጠናክረው ቀጠሉ ፡፡

አማካይ ክፍል ተጫዋቹ የአብስራ ተስፋዬ ከ አዳማ ጋር በነበረው ጨዋታ ኮከብ ሆኖም ለመመረጥ በቅቷል ፡፡ ሶስተኛ ጨዋታቸውን መስከረም 23 ቀን2014 ከ ባህርዳር ጋር ያደረጉት ፈረሰኞቹ በቅርቡ ወደ ዋናው ቡድን ባደገው ወጣቱ ጋዬ መላኩ አማካኝነት ሁለት ጎሎች እንዲሁም በተከላካዩ ፍሪምፖንግ ሜንሱ አንድ ጎል በድምሩ የጣና ሞገዶቹን ባህርዳሮችን ሶስት ለዜሮ በሆነ ወጤት ረተዋል፡፡

ሁለት ጎሎችን መረብ ላይ ከማሳረፍ ባሻገር ሜዳ ላይ ድንቅ እንቅስቃሴ ሲያደርግ የነበረው ጋዬ መላኩ ከባህርዳር ጋር በነበረው ጨዋታ ኮከብ ተብሎ ለመሸለም ችሏል፡፡ ጋዬ መላኩ የፈረሰኞቹ ወደፊቱ አኩሪ ኮከብ እንደሚሆንም ፍንጭ የታየበት ነበር፡፡ በዚህ ጨዋታ ፈረሰኞቹ ሶስት ተከታታይ ጨዋታዎች በማሸነፍ በድምሩ ሰባት ጎሎችን መረብ ላይ ማሳረፍ የቻሉበት ነበር፡፡

ቅዱስ ጊዮርጊስ መስከረም 26 ቀን 2014 ከመከላከያ ጋር በነበረው የግማሽ ፍጻሜ ጨዋታ 90 ደቂቃውን ባዶ ለባዶ በሆነ ውጤት በማጠናቀቁ ጨዋታው ወደ መለያ ምት በማምራቱ በመከላከያ ተሸንፈው ለ7ኛ ጊዜ ዋንጫውን ለማንሳት የነበረው ህልም ሳይሳካ ቀርቷል፡፡

ቅዱስ ጊዮርጊስ በአዲስ አባበ ከተማ ዋንጫ የዘንድሮውን ጨምሮ ለ12ኛ ጊዜ ተሳትፎ 6 ጊዜ ዋንጫው በማንሳት የበላይነት ታሪክ አለው ፡፡ ስለሆነም ፈረሰኞቹ ይህን ውድድር በዋናነት ዋንጫ ለማንሳት ሳይሆን ጥቅምት ወር መጀመሪያ ላይ ይጀመራል ተብሎ ለሚጠበቀው የኢትዮጵያ ፕሪሚየር ሊግ እንደ አቋም መፈተሻ ተጠቅመውበታል፡፡

ይህ የአዲስ አበባ ከተማ ዋንጫ ፈረሰኞቹ በቅድመ ውድድሩ ወቅት ያደረጓቸውን ዝግጅቶች ድክመትና ጥንካሬዎቹን ለመፈተሽም አጋጣሚዎችን ያገኙበትና አቋማቸውን ለመፈተሽ ያስቻላቸው ነበር፡፡ በጨዋታው የተሳተፉ ታዳጊ ተጫዋቾቻችን ያሉበትን ወቅታዊ ብቃትና ችሎታ በአደባባይ ለማየት እንዲችሉ እድል ያገኙበትም ነበር፡፡ ወጣት ልጆቻችን እጅግ አስደናቂ የሜዳ ላይ እንቅስቃሴ አሳይተውናል፡፡

በታዳጊዎቹ ላይ ያየነው ተስፋ ሰጪ የሆኑ እንቅስቃሴዎች ወደ ፊት ቅዱስ ጊዮርጊስ በብሄራዊ ቡድን ደረጃ ውጤታማ እና ተጽእኖ ፈጣሪ ተጫዋቾችን ማፍራቱን እንዳላቆመ አረጋግጧል፡፡ በዚህ የውድድር መድረክ ላይ ካለፉት ዓመታት በተሻለ ቁጥራቸው የበረከቱ ወጣት ተጫዋቾችን ማሳተፍ ተችሏል፡፡ ሁሉም በተሰለፉባቸው ጨዋታዎች አስደናቂ በሆነ ሁኔታ ብቃታቸውን አሳይተዋል በቀጣይ ውድድሮችም ልምድ ካላቸው ተጫዋቾች ጋር የበለጠ ማቀናጀትና ማዋሃድ ከተቻለ የተሻለ ነገር እንደሚያሳዩን አመላክቶናል፡፡ የቅዱስ ጊዮርጊስ ተስፋ በወጣቶች ላይ በመሆኑ ተተኪዎች ከታላላቆቹ ጋር እየተሰባጠሩ ብዙ ልምድ እንዲያገኙ ሰፊ እድል ማመቻቸት እንዳለብንም በሚገባ አሳይቶን ያለፈ ክስተት ሆኗል፡፡



# የኢትዮጵያ ፕሪምየር ሊግ

በካፑካ ሣንጆርጅ

ከ1936 ዓ.ም እስከ 1989 ዓ.ም ድረስ ሲካሄድ በቆየው የኢትዮጵያ ሻምፒዮን በርካታ የሃገራችን ቡድኖች በዞን ተከፋፍለው ያደርጉት የነበረው ውድድር በ1990 ዓ.ም የስያሜ እና የቅርጽ ለውጥ በማድረጉ በርካታ ቡድኖች በተሏዙሮው ጨዋታ ለከፍተኛ ወጪ በመዳረጋቸው የአቅም መዳከም ሊፈጠርባቸው ከመቻሉ በላይ በጣም በሚያሳዝን መልኩ በሊጉ የ21 ዓመታት ቆይታ ከተካፈሉ 48 ቡድኖች መካከል 50% ያህሉ ፈርሰዋል፡፡

በሌላ አቅጣጫ ከ1990 ዓ.ም ወዲህ የክልል ቡድኖች አቋም የስፖርት ታዳሚውን ለሁለት ክፍሎ ሲያከራክር ቆይቷል፤ በአንደኛው ወገን የሚገኙት በካምቦሎጆ ቋንቋ “ደረጃ መዳቢ” መሆናቸውን ሲገልፁ የተቀሩት “የገንዘብ አቅማቸው ቢጠናከር እምቅ አቅም ይኖራቸዋል” የሚል ሃሳብ ከማቅረባቸው በላይ እንደ ምሳሌ ሐዋሳ ከነማ ያነሳቸውን ሁለት ዋንጫዎች ያነሳሉ፡፡

የሃያ አንድ ዓመታት ቆይታ ያደረገው ፕሪምየር ሊግ በሆሊውድ ብራድ ፒት እንደተወነበት “Series cause of Benjamin button” ፊልም ላይ እንዳለው ገፀ ባህሪ ከውልደቱ እርጅና የተጫጫነው ይመስላል፡፡ በ1990 ዓ.ም የተጀመረው የኢትዮጵያ ፕሪምየር ሊግ ስታትስቲክስ ከማግኘት በ1888 ዓ.ም በአድዋ ጦርነት የተሰዉ አርበኞች ቁጥርን ማወቅ ይቀላል፡፡ የሊጉን መረጃዎች የሚሰበስብ እና ይፋ የሚያደርግ አካል እንዲሁም ሥራዬ ብሎ ሊጉን የሚከታተል ሚዲያ ባለመኖሩ በአፈ ታሪክ ብቻ የሚነገር የጥንታዊ ሊግ ባለቤት እንድንሆን አድርጎናል፡፡ የሃገራችን ፕሪምየር ሊግ የራሱ የሆነ ባህል፣ እሴት፣ ይፋዊ የሆነ አርማ (Logo)፣ በተሳተፍኩበት፣ ባየሁት ተብሎ የሚጓጓለት የፉክክር ድባብ፣ ሽልማት እና ጠንካራ የህዝብ ግንኙነት የሌለው እንዲሁም ከጥቂት ቡድኖች በስተቀር አብዛኛዎቹ ተሳታፊዎች የራሴ የሚሉት ደጋፊ እና መለያ የሌላቸው ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡

ከ1990ዎቹ አጋማሽ ወዲህ በአብዛኛዎቹ ጋዜጠኞቻችን መሪነት በጋዜጦች፣ በንፋስ ድምፅ /Radio/፣ በምስለ መስኮት / Television/ እና በምስለ ሰብስብ ገበቴ /Satellite dish/ በመታገዝ ሙሉ ለሙሉ ለማለት በሚያስደፍር መልኩ የባህር ማዶ ዜናዎች ተርጓሚ ሆነው ቆይተዋል፤ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ያለውን ለውጥ ማመስገናችንን ሳንዘነጋ፡፡ በአንድ ወቅት በተደረገ ጥናት ከ1990 ዓ.ም እስከ 2002 ዓ.ም በቴሌቪዥን የቀጥታ ስርጭት ለማግኘት የቻሉ የኢትዮጵያ ፕሪምየር ሊግ ጨዋታዎች አምስት ሲሆኑ በአንፃሩ በ2002ዓ.ም ብቻ 38 የእንግሊዝ ፕሪምየር ሊግ፣ 27 የዩሮፓ ሻምፒዮንስ ሊግ፣ የአፍሪካ እና የዓለም ዋንጫ ጨዋታዎች ሽፋን ተሰቷቸዋል፡፡

የጊዜ ዕጣ ፈንታ የሚያንገላታው የኢትዮጵያ ፕሪምየር ሊግ የሚጀመርበት ቀንን ቀድሞ ለማወቅ ቢቻልም መቼ እንደሚጠናቀቅ የሚታወቀው በመጨረሻው ሳምንት ጨዋታ እለት እንጂ በቅድሚያ ሲጀመር በተዘጋጀው መርሃ ግብር አይደለም፡፡ በመካከለኛው ምስራቅ በማንኛውም ሰዓት ግጭት ሊጀመር እንደሚችለው ሁሉ የኢትዮጵያ ፕሪምየር ሊግ በማንኛውም ጊዜ በብሔራዊ ቡድን ዝግጅት፣ በበአላት፣ በመጥፎ የአየር ፀባይ እንዲሁም በአንድ ወቅት እንደተከሰተው በአንድ የፕሪምየር ሊግ ቡድን ውስጥ በሚጫወት ተጫዋች ሰርግ ምክንያት ሊቋረጥ ይችላል፡፡

በሌላ አቅጣጫ የዳኝነት ጉልህ ስህተት፣ የአስተዳደር ችግር፣ በደጋፊ እና በህግ ዘበኛ / Police/ መካከል አለመከባበር፣ የተጫዋቾች ፅብ አነሳሽነት የኢትዮጵያ ፕሪምየር ሊግን የነውጥ ማዕከል ሲያደርጉት ቆይተዋል፡፡ ለጤና አስቸጋሪ የሆነው ስታዲየማችን አረጋውያንን፣ ሴቶች እና ሕፃናትን ወደ ሜዳ አይጋብዝም፡፡ የዓለማችን ታላላቅ ቡድኖች ዓመታዊ ገቢ 1/3ኛውን የሚይዘው የስታዲየም ገቢ ቢሆንም ይህ በሃገራችን ሲሆን ለማየት እንዳንችል ካደረጉን ምክንያቶች መካከል አንዱ የውድድር መርሃ ግብር አወጣጥ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡

በ2008 ዓ.ም በአዲስ አበባ ስታዲየም 78 ጨዋታዎች የተደረጉ ሲሆን እነዚህ ጨዋታዎች ሰባት ያህሉ ቅዳሜ፣ አስራ ሁለት ጨዋታዎች እሁድ እንዲሁም ሃምሳ ዘጠኝ ጨዋታ እንደ ማክሰኞ እና ረቡዕ ባሉ የስራ ቀናት የተከናወኑ መሆናቸው ስፖርት ታዳሚው ወደ ሜዳ ለመምጣት እንዲቸገር ሲያደርጉት ተስተውለዋል፤ እነዚህ እና ሌሎች በርካታ ምክንያቶች “ከምንም” ተፈጥሮ “ምንም” የሆነ ፕሪምየር ሊግ እንዳለን ያሳዩናል፡፡

### የተጫዋቾች መኮብለል!

1989 ዓ.ም የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን ከሞሮኮ አቻው ጋር ለሚጠብቀው ጨዋታ ከተለያዩ ቡድኖች ያሰባሰባቸውን ተጫዋቾች በሆቴል በማስቀመጥ ዝግጅቱን በአዲስ አበባ ስታዲየም ሲያከናውን ሰነባበተ፡፡ የጨዋታው ቀን እየተቃረበ ሲመጣ ከአዲስ አበባ ወደ ካዛብላንካ ቀጥታ በረራ ባለመኖሩ የብሔራዊ ቡድኑ አባላት ጣሊያን ሮም ላይ ትራንዚት ለማድረግ ቢገደዱም ቀጣይ ከሮም ወደ ካዛብላንካ የቡድኑ አባላት በረራ ለማድረግ ሳይችሉ ቀሩ ምክንያቱም በኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን ስብስብ ከተካተቱት 18 ተጫዋቾች መካከል 16 ያህሉ ሮም ላይ በመኮብለላቸው ነበር፡፡

በርግጥ ከቡድኑ አባላት ውስጥ 10 ያህሉ አስበውበት የጠፉ ሲሆን እዛው ጣሊያን ላይ ሲቀሩ ስድስቱ ያረፉበት ሆቴል ውስጥ ጓደኞቻቸውን በማጣታቸው ለፍለጋ ወጥተው በዛው የቀሩ ናቸው፡፡ ከቅዱስ ጊዮርጊስ ዘሪሁን ሸንገታ እና ደሳለኝ ገብረጊዮርጊስ በታማኝነት ወደ ሃገራቸው ከተመለሱ ከቀናት በኋላ ወትሮም የመኮብለል ዕቅድ ያልነበራቸው በስህተት ጣሊያን ላይ የቀሩት 6 ተጫዋቾች ወደ ሃገራቸው ተመለሱ፡፡

ከስድስቱ ተጫዋቾች መካከል የቅዱስ ጊዮርጊሶቹ ፋሲል ተካልኝ፣ አሸናፊ ሲሳይ፣ አንተነህ አላምረው እና ፀጋዬ ባቲ ይገኙበታል፡፡ ተጫዋቾቹ ምንም እንኳን በፈቃዳቸው ወደ ሃገራቸው ቢመለሱም የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን (የኢ.እ.ፌ) ከቡድናቸው ጋር ተቀላቅለው እንዳይጫወቱ አገዳቸው፡፡

ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን በርካታ ተጫዋቾችን ለማስመረጥ ከቻሉ ቡድኖች መካከል ቀዳሚው የሆነው የቅዱስ ጊዮርጊስ ስፖርት ማህበር ከቡድኑ የተለዩት ተጫዋቾች ከፍተኛ የሆነ ክፍተት ፈጠሩበት፡፡ በሌላ አቅጣጫ የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራ ፋብሪካ ለቡድኑ የሚያወጣው ወጪ ከዓመት ዓመት እየናረ በመምጣቱ ቡድኑ የህልውና ፈተና ተጋርጦበታል፡፡

በፈረሰኞቹ ላይ የተፈጠረው ወቅታዊ ችግር ስር ሰዶ እንዳይሄድ የችግር አስወጋጅ ኮሚቴ ቢቋቋምም ነገሮች መስመር ከመያዝ ይልቅ እየተወሳሰቡ፤ በሚስጥር ተይዘው የነበሩ ችግሮች እየፈነዱ የአደባባይ ሚስጥር መሆናቸውን ቀጠሉ፡፡ በተጫዋቾች እጥረትና ከሜዳ ውጪ በተለያዩ ችግሮች የተተበተበው ቡድን ለአመራሮቹ ፈታኝ ከመሆኑ በተጨማሪ በሜዳ ላይ በሚሰጥ ስልጠና ብቻ ውጤት ማምጣት አዳጋች እስከመሆን ደረሰ፡፡

በነዚህና መሰል ውስብስብ ችግሮች ውስጥ የገባው ቡድን መጋቢት 14 ቀን 1989ዓ.ም በአፍሪካ ሻምፒዮንስ ሊግ ከግብፁ ጠንካራ ቡድን ዛማሊክ ጋር ላለበት ጨዋታ በቅጣት ላይ የሚገኙት ተጫዋቾቹ ምህረት ተደርጎላቸው ሃገራቸውን እንዲወክሉ ለኢ.እ.ፌ. አመራሮች ጥያቄ ቢያቀርቡም አዎንታዊ ምላሽ ሳያገኝ ቀረ፡፡

በጉዳትና በቅጣት እየታመሰ የሚገኘው ቡድን ዛማሊክን ለመግጠም ሳይሟላ ወደ ሜዳ ቢገባም በሰላሳ አንደኛው ደቂቃ ላይ በድንቅ የመሃል ሜዳ አጨዋወቱ የሚታወሰው ተስፋዬ ዑርጌቾ ባስቆጠራት ግብ 1-0 ለመምራት ቢችልም ዛማሊኮች አቻ የምታደርጋቸውን ግብ አስቆጥረው በአዲስ አበባ ስታዲየም የተደረገው ጨዋታ 1-1 ተጠናቀቀ፤ ቀደም ሲል ካይሮ ላይ በተደረገው ጨዋታ ዛማሊክ 2-0 አሸናፊ የነበረ በመሆኑ ቅዱስ ጊዮርጊስ በአፍሪካ መድረክ ከነበረበት ውድድር በጊዜ ሊገለል ቻለ፡፡

ከኢንተርናሽናል የውድድር መድረክ በጊዜ የተሰናበተው ቅዱስ ጊዮርጊስ ሙሉ ትኩረቱን ወደ ሃገር ቤት ውድድር በመመለስ በሻምፒዮናው ላይ ተነጥቆ የነበረውን የመሪነት ስፍራ ለማስመለስ ጠንካራ ስራ መስራት ቢጠበቅበትም በጉዳት እና በእገዳ ከቡድኑ የተለዩ ተጫዋቾችን ክፍተት ለመሸፈን አዳጋች ሆነ፡፡

### ድንገተኛው ቆረጣ!

የ1989 ዓ.ም የኢትዮጵያ ሻምፒዮና የአንደኛ ዙር የውድድሩ መርሃ ግብርን ለማጠናቀቅ ቅዱስ ጊዮርጊስ የመጨረሻ ጨዋታውን ከአሜድላ ጋር ማከናወን ይጠበቅበታል፡፡ ይህንን ጨዋታ በድል ማጠናቀቅ ከቻለ ደረጃውን ከ4ኛ ወደ 2ኛ ከፍ በማድረግ ለዋንጫ ያለውን ተስፋ ያለመልማል፡፡ አሜድላ በተከታታይ ባደረጋቸው አምስት ጨዋታዎች ለተጋጣሚዎቹ በቀላሉ እጁን ሊሰጥ የቻለ በመሆኑ ከሊጉ ላለመውረድ እየታገለ የሚገኝ በመሆኑ ቅዱስ ጊዮርጊስ ከአሜድላ ላይ ሶስት ነጥብ ብቻ ሳይሆን በርከት ያለ ግብ አስቆጥሮ ያለበትን የግብ ክፍያ ችግር ያቃልላል የሚለው ግምት የአብዛኛው የስፖርት ቤተሰብ የነበረ ቢሆንም ጨዋታው በአሜድላ 3-1 አሸናፊነት ተጠናቀቀ፡፡ በዚህ ውጤት መሠረት ፈረሰኞቹ የአንደኛውን ዙር በስድስተኛ ደረጃ አጠናቀቁ፡፡

የፈረሰኞቹ ደጋፊዎች ቡድናቸው ከዋንጫ ሽሚያ እየራቀ በመምጣቱ ቅሬታ ቢሰማቸውም የቡድናቸው ውጤት ማሽቆልቆል ከበስተኋላው ሌላ ችግር አስከትሎ እንደሚመጣ ግን ግንዛቤ አልነበራቸውም፤ እንዴትስ ሊገምቱ ይችላሉ? የኢ.እ.ፌ የውድድር ቅርፅ ለውጥ ለማድረግ ሲያስብ በጠቅላላ ጉባዔ ላይ በማቅረብ ሁሉም ቡድኖች ከተወያዩበት በኋላ እንዲፀድቅ የማድረግ ልምድ ቢኖረውም በ1989 ዓ.ም የተከሰተው ከዚህ ይለያል ቡድኖች የውድድር መርሃ ግብራቸውን ባጋመሱበት፣ ሻምፒዮን የሚሆነውና በመውረድ ስጋት ላይ ያሉ ቡድኖች እየለዩ በነበሩበት ወቅት ከአዲስ አበባ አራት ከየክልሉ ሁለት-ሁለት ቡድኖች የሚካፈሉበት በአይነቱ ለየት ያለ ውድድር እንደሚጀመር የሚገልፅ መመሪያ የክልል ፌዴሬሽን አመራሮች እንዲደርሳቸው ተደረገ፡፡ በዚህ ወቅት ቅዱስ ጊዮርጊስ ስድስተኛ ደረጃ ላይ ከመገኘቱ በተጨማሪ በደረጃው ግርጌ የሚገኙ ቡድኖች ተቆርጠው ሊቀሩ መሆኑ ስለገባቸው ግራ ተጋቡ፡፡

ይህ ቡድኖች ሳይዘጋጁ ቆርጦ የመጣል አባዜ ለኢትዮጵያ እግር ኳስ አዲስ አይደለም እንዴት? የሚል ጥያቄ ከተነሳ በ1984 ዓ.ም የአዲስ አበባ ሻምፒዮና እየተደረገ በነበረበት ወቅት ድንገት ከአንደኛ እስከ ስምንተኛ ደረጃ ያጠናቀቁት ቡድኖች በቀጣይ ዓመት በብሔራዊ ፌዴሬሽኑ ስር እንደሚወዳደሩ እንዲሁም የተቀሩት እዛው ባሉበት እንደሚቀሩ ቀድመው ግንዘቤ ሳይኖራቸው ተቆርጠው የቀሩበት የውድድር ዓመት ምላሽ ይሆንናል፡፡

የቅዱስ ጊዮርጊስ አመራሮች አዲስ የወጣው መመሪያ በቡድናቸው ላይ ያነጣጠረ ሴራ እንደሆነ ስለተረዱት ታሪካዊው ቡድን በታችኛው ዲቪዝዮን ተቆርጦ እንዳይቀር መፍጨርጨር ጀመሩ፡፡ በቡድኑ ውስጥ ያለውን ችግር አፅድተው በታገዱበት ተጫዋቾች ምክንያት የተፈጠረውን ክፍተት አስተካክለው ጠንካራ ተፎካካሪ ሆነው ለመቅረብ ላይና ታች መሯሯጥ ጀመሩ፡፡

ለቅዱስ ጊዮርጊስ በእንደዚህ አይነት ፈተናዎች ወቅት በስኬት ማለፍ አዲስ አይደለም፤ ብዙ መሰናክሎች ተጋርጠውበት በአስደናቂ ሁኔታ እንዳለፋቸው የታሪክ ድርሳናት የሚያስታውሱት ነው፡፡ ዛሬም እንደተናንቱ ያሉበትን ችግሮች ተቋቁሞ ከፊቱ የሚያገኛቸውን ተጋጣሚዎች እያሸነፈ ለስኬት መብቃት ይጠበቅበታል፡፡

በ1989 ዓ.ም የለመደውን ዋንጫ አለማንሳቱ ችግር የለውም፣ ሁለተኝነትም አስደሳች ነው፤ ሶስተኛ እና አራተኛ ደረጃ ይዞ ማጠናቀቅ ከወርቅ የበለጠ ዋጋ እንዳለው ቢገመትም ወቅታዊ የቡድኑ ደረጃ ስድስተኛ በመሆኑ ከበላዩ የሚገኙ ቡድኖች ጋር ያለውን የነጥብ ልዩነት ማጥበብ ይኖርበታል፡፡ ይህንን ህልማቸውን እውን ለማድረግ የፈረሰኞቹ ተጫዋቾች ተሰባስበው በመመካከር የግል ችግራቸውን ወደጎን በማለት ይህንን ታላቅ ቡድን ለማትረፍ ቃል ተገባቡ፡፡

ተጫዋቾቹ ምክክር ካደረጉ በኋላ መጋቢት 28 ቀን 1989 ዓ.ም የመጀመርያ ጨዋታቸውን ከመድህን ጋር አከናውነው 0-0 በሆነ ውጤት ተለያዩ በመቀጠል ሚያዝያ 2 ቀን 1989 ዓ.ም ከኪራይ ቤት ጋር የነበራቸውን ጨዋታ 1-1 በሆነ አቻ ውጤት በማጠናቀቃቸው ሦስት ነጥብ የማግኘት ህልማቸው ለተከታታይ ሁለት ጨዋታ ዕውን ሳይሆን ቀረ፤ ሆኖም ከላይ ያሉት ቡድኖች ሽንፈትን እያስተናገዱ በመሆናቸው ቅዱስ ጊዮርጊስ በሁለት ጨዋታ ባገኘው ሁለት ነጥብ ታግዞ የነጥብ ልዩነቱን ለማጥበብ ቻለ፡፡ አሁን ሜዳ ላይ እየታየ የሚገኘው ቡድን እውነተኛ የቅዱስ ጊዮርጊስ ተምሳሌት ባይሆንም ለመምሰል እየጣረ ነው፡፡

ወደ ገፅ 5 ዞሯል



## የፔፕሲ ገጽ

የኢትዮጵያ...

ከገፅ 4 የዞረ

በቀጣይ ሚያዚያ 15 ቀን 1989 ዓ.ም ባደረገው ጨዋታ በጠንካራ አቋም ላይ የሚገኘው መብራት ሃይልን በስንታየሁ ጌታቸው(ቆጬ) ግብ 1-0 አሸነፈ፡፡ በተከታታይ ሶስት ጨዋታ ሳይሸነፍ በመጓዙ በቡድኑ ላይ ከፍተኛ የሆነ መነቃቃት እየታየ ባለበት ወቅት ግን የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን በነበረበት ኢንተርናሽናል ጨዋታ ምክንያት ውድድሩ ተቋረጠ፡፡

በኢንተርናሽናል ጨዋታ ምክንያት ተቋርጦ የነበረው ውድድር ሰኔ 05 ቀን 1989 ዓ.ም ሲጀመር ኢትዮጵያ ቡናን የገጠመው ቅዱስ ጊዮርጊስ በፍስሃ ቢጋሻው ግብ 1-0 በማሸነፍ ደረጃውን ወደ አራተኝነት ከፍ አደረገ፡፡ የፈረሰኞቹ ደጋፊዎች ቡድናቸው ደረጃውን ለማሻሻል በመቻሉ መጠነኛ መረጋጋት ቢታይባቸውም በቀጣይ ጨዋታ ዳግም ነጥብ በመጣሉ ስጋት ውስጥ ተመልሰው ገቡ፡፡

የውድድር መርሃ ግብሩ ማጠናቀቂያ በሆነው ጨዋታ ቅዱስ ጊዮርጊስ የራሱን እድል በራሱ ለመወሰንና በቀጣይ ዓመት ይጀመራል የተባለውን ሊግ ለመቀላቀል ወሳኝ ጨዋታ ከግምሩክ ጋር ይጠብቀዋል፡፡

ግምሩክ ላለመውረድ በመጫወት ላይ የሚገኝ ቡድን ስለሆነ እንዲሁም ውጤቱ ለፈረሰኞቹ ካለው ወሳኝነት አንፃር የአሸናፊነት ግምቱ ወደ ቅዱስ ጊዮርጊስ ያደላ ቢሆንም ጨዋታው በተጀመረ በሁለተኛው ደቂቃ ላይ እንዳለ ብርቄ ግብ አስቆጥሮ ግምሩክ 1-0 ሊመራ ቻለ፡፡

በተቆጠረባቸው ግብ ያልተደናገጡት ፈረሰኞች በድንቅ የግብ አጨራረስ ብቃቱ በሚታወቀው ስንታየሁ ጌታቸው (ቆጬ) አማካኝነት በሃያ አንደኛው ደቂቃ ላይ አቻ የምታደርጋቸውን ግብ አስቆጠሩ፡፡

ከዚህች ግብ መቆጠር በኋላ ፈረሰኞቹ በደጋፊዎቻቸው ህብረ ዜማ ታጅበው ተጨማሪ ግብ ለማስቆጠር ቢጣደፉም ያሰቡትን ለማሳካት ሳይችሉ እረፍት 1-1 በሆነ ውጤት ለመለያየት ቻሉ፡፡ ከእረፍት መልስ በሃምሳ ስድስተኛው ደቂቃ መሐመድ ኑር ለግምሩክ ሁለተኛውን ግብ አስቆጠረ፡፡

ጨዋታው በጉምሩክ 2-1 መሪነት በቀጠለበት ሰዓት የፈረሰኞቹ ግብ ጠባቂ የጉምሩክ ተጫዋች በሆነው ያሬድ ጌታቸው ላይ ያልተገባ አጨዋወት በመጫወቱ የመሃል ዳኛ የነበሩት አቦነህ አሻግሬ የሰጡትን ፍፁም ቅጣት ምት ስለሺ ግደይ አስቆጥሮ ጨዋታው በግምሩክ 3-1 አሸናፊነት በመጠናቀቁ ቅዱስ ጊዮርጊስ በአሳዛኝ ሁኔታ በቀጣይ ዓመት በሚጀመረው ሊግ እንደማይካፈል ተረጋገጠ፡፡

የፈረሰኞቹ ደጋፊዎች፣ አመራሮች እና የቡድኑ አባላት ጥልቅ የሆነ ሃዘን እና ቁጭት ከፊታቸው ላይ እየተነበበባቸው የአዲስ አበባ ስታዲየምን ለቀው ለመውጣት ተገደዱ፡፡

### ከከፍተኛ ዲቪዚዮን እስከ ፕሪምየር ሊግ

በ1990 ዓ.ም የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሊግ በሚል ስያሜ የተጀመረው ውድድር ከአዲስ አበባ መብራት ሃይል፣ ኢትዮጵያ መድህን እና ኢትዮጵያ ቡናን፤ ከደቡብ ኢትዮጵያ ሃዋሳ ከነማ፤ ከመቀሌ ጉና ንግድ፤ ከአማራ ክልል ኮምቦልቻ ጨርቃጨርቅ፤ ከኦሮሚያ ፐልፕ እና ወረቀት እና ከድሬደዋ መስተዳድር ድሬደዋ ጨርቃ ጨርቅን አካቶ ጅማሮውን አደረገ፡፡

በመጀመርያው የውድድር ዓመት የመብራት ሃይል ስፖርት ቡድን በአሰልጣኝ ሃጎስ ደስታ እየተመራ አሸናፊ በመሆን ባለታሪክ ለመሆን ቻለ፡፡

በ1989 ዓ.ም ባስመዘገበው ውጤት በአዲስ አበባ በከፍተኛ ዲቪዝዮን ለመቆየት የተገደደው ቅዱስ ጊዮርጊስ በ1990 ዓ.ም መስከረም ወር ላይ ገና ዝግጅቱን በአግባቡ ሳያጠናቅቅ በግዴታ መልክ በኢትዮጵያ ጥሎ ማለፍ ውድድር ላይ እንዲካፈል ተደርጎ በአየር መንገድ እንዲሁም ለገቢ ማሰባሰቢያ በተዘጋጀ የወዳጅነት ጨዋታ በኢትዮጵያ ቡና በመሸነፉ ስፖርት ተመልካቹም ሆነ በአንዳንድ የሚድያ አካላት ቅዱስ ጊዮርጊስ እንዳበቃለትና ብሔራዊ ሊጉን በቀጣይ ዓመት የመቀላቀል ተስፋ እንደሌለው ተደርጎ ቢታሰበም የዝግጅት ጊዜውን በአግባቡ አጠናቆ በአዲስ አበባ ከፍተኛ ዲቪዝዮን ሻምፒዮና ላይ በጥሩ ብቃት ሲመጣ ተስፋ በመቁረጥ ርቀው የነበሩ ደጋፊዎች መጠነኛ እርካታ በማግኘታቸው ዳግም ወደ ካምቦሎጆ ተመለሱ፡፡

> “በአንድ ወቅት እንደተከሰተው በአንድ የፕሪምየር ሊግ ቡድን ውስጥ በሚጫወት ተጫዋች ሰርግ ምክንያት ሊቋረጥ ይችላል፡፡”

በ1990 ዓ.ም በተደረገው የአዲስ አበባ ከፍተኛ ዲቪዚዮን ሻምፒዮና ቅዱስ ጊዮርጊስ አንድም ጨዋታ ሳይሸነፍ ዋንጫ ለማንሳት ከመቻሉ በተጨማሪ ስንታየሁ ጌታቸው (ቆጬ) በ20 ግብ ኮከብ ግብ አግቢ፣ ፋሲል ተካልኝ በኮከብ ተጫዋችነት ለመመረጥ ቻሉ፡፡

በቡድን ደረጃ ከተገኘው የሻምፒዮንነት ክብር በተጓዳኝ ቅዱስ ጊዮርጊስ የፀባይ ዋንጫ አሸናፊ ለመሆን በመቻሉ የደጋፊዎቹን ደስታ እጥፍ ድርብ ሆነ፡፡ በዚህ ውጤት መሰረት ፈረሰኞቹ ወደ ብሔራዊ ሊጉ ለመግባት በድሬዳዋ አስተናጋጅነት በተዘጋጀው የሱፐር ሊግ ውድድር ተካፋይ መሆናቸውን አረጋገጡ፡፡

ድሬዳዋ ላይ በተዘጋጀው የሱፐር ሊግ ውድድር ቅዱስ ጊዮርጊስ የምድቡን የመጀመርያ ጨዋታ በሙገር ሲሚንቶ 2-1 በሆነ ውጤት ቢሸነፍም ቀሪዎቹን አራት የምድብ ጨዋታዎች በተከታታይ ለማሸነፍ በመቻሉ ሙገር ሲሚንቶን በመከተል ከምድቡ የሁለተኝነት ደረጃ በመያዝ ግማሽ ፍፃሜውን ተቀላቀለ፡፡ በግማሽ ፍፃሜው ሙገር ሲሚንቶ ወላይታ ቱሳን በመርታት እንዲሁም ቅዱስ ጊዮርጊስ የድሬደዋ ምድር ባቡርን 5-1 በሆነ ሰፊ ውጤት በመረምረሙ የዋንጫ ተፋላሚ ለመሆን ከመቻሉ በተጨማሪ በ1991 ዓ.ም ሁለቱ የዋንጫ ተፋላሚዎች በኢትዮጵያ ብሔራዊ ሊግ ተካፋይ መሆናቸውን አረጋገጡ፡፡ ለዋንጫ ሽሚያ በተደረገው ጨዋታ ቅዱስ ጊዮርጊስ 3-1 በሆነ ውጤት ሙገር ሲሚንቶን አሸንፎ የሱፐር ሊጉ አሸናፊ ሲሆን በተደረገው የኮከቦች ምርጫ ልክ እንደ አዲስ አበባ ከፍተኛ ዲቪዝዮን ሻምፒዮና ፋሲል ተካልኝ ኮከብ ተጫዋች ስንታየሁ ጌታቸው (ቆጬ) ኮከብ ግብ አግቢ በመሆን ሊሸለሙ ቻሉ፡፡

በዚህ ዓመት ደጋፊው በአዲስ አበባም ሆነ በድሬዳዋ ውድድር የከፈለው መስዋዕትነት ታሪክ ሊዘነጋው የማይችለው ነው፡፡ በ1991 ዓ.ም ቅዱስ ጊዮርጊስ ከብሔራዊ ሊግ ወደ ፕሪምየር ሊግ የስያሜ ለውጥ ያደረገውን ውድድር በተቀላቀለበት ዓመት ከመብራት ሃይል ጋር አድርጎት በነበረው ግጥሚያ በኤሊያስ ጁሃር ግብ 1-0 ከመሸነፉ በስተቀር ዓመቱን ያለምንም ሽንፈት ከማጠናቀቁ በላይ ሁለት ጨዋታ እየቀረው የፕሪምየር ሊጉ ሻምፒዮን መሆኑን አረጋገጠ፡፡

ቅዱስ ጊዮርጊስ በዚህ መልኩ የተቀላቀለውን ሊግ ከ1991ዓ.ም እስከ 2013 ዓ.ም ባደረገው ተሳትፎ ለአስራ አራት ጊዜያት ያክል (በ1991 ዓ.ም፣ 1992 ዓ.ም፣ 1994 ዓ.ም፣ 1995 ዓ.ም፣ 1997 ዓ.ም፣ 1998 ዓ.ም፣ 2000 ዓ.ም፣ 2001 ዓ.ም፣ 2002 ዓ.ም፣ 2004 ዓ.ም፣ 2006 ዓ.ም፣ 2007 ዓ.ም፣ በ2008 ዓ.ም እና 2009 ዓ.ም) ሻምፒዮን መሆኑን አረጋገጠ፡፡

